የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ)

**SOLIDARITY COMMITTEE FOR ETHIOPIAN POLITICAL PRISONERS (SOCEPP)**

# በኢትዮጵያ ስላለው የሰብአዊ መብት እረገጣና ይህን ለማጋለጥ በጋራ ሊካሄድ ስለሚገባው እንቅስቃሴ ለመወያየት ሕዝባዊ ስብሰባ - በለንደን

ቀንና ሰዓት፡ ህዳር 6፣ 2007 ዓ. ም. ከቀኑ 8.00 ሰዓት ጀምሮ (15 November 2014, from 2.00pm)

ቦታው፡ የኢትዮጵያዊያን ተራድዖ ማህበር የስብሰባ አዳራሽ (ECB Hall, 2A Lithos Rd, NW3 6EF)

---

በሀገራችን በኢትዮጵያ የሚካሄደው የሰብአዊ መብት ረገጣ ቋንቋ፣ አካባቢ፣ ሀይማኖት፣ ጾታ፣ ሙያ፣ የተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት ወገንተኝነት ሳይለይ አፈና ገድያው፣ ማሳደድ፣ እስሩ የሁሉንም በር እያንኳኳ ነው። የሚያስከትለው ሀዘንና ጉስቁልና፣ ሰቆቃና ስጋት የሁላችንም ልብ ያደማል። ስለዚሁ ሁላችንንም ስለሚያሳስበው የሰብአዊ መብት እረገጣ፣ ይህንንም ለማጋለጥና ለማስወገድ በጋራ ልናካሂድ ስለሚገባን እንቅስቃሴ በለንደንና አካባቢው የምንኖር ኢትዮጵያዊያን ውይይት እንድናካሂድ አንድ ሕዝባዊ ስብሰባ አዘጋጅተናል።

በስብሰባው ላይ የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ፕሬዚዴንት የሆኑት ታዋቂው የሰብአዊ መብት ተሟጋች እና በዚህም ሥራቸው በካናዳ የተለያዩ ሽልማቶች ተቀብለው በጎ ምግባራቸው ዕውቅና ያገኘው፣ ገጣሚ ዓሊ ሁሴን በክብር እንግድነት ይገኛሉ። በቅርቡ ከየመን ታፍነው በመወሰድ በወያኔ እስር ቤት የሚገኙት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ ባለቤት፣ ከድምፃችን ይሰማ፣ ከግንቦት ሰባት፣ ከሞረሽ እና ከኢሕአፓም ተወካዮች ተገኝተው በውይይቱ ይሳተፋሉ። የሰብአዊ መብት እረገጣ መገለጫ የሆኑት ግድያ፣ እስር፣ አፈና፣ ማሳደድና ሌሎችም በአገዛዙ የሚካሄዱ እኩይ ተግባራት ሁላችንንም የሚያሳስቡ የጋራ ችግሮቻችን ናቸው ብለን በማመን እርስዎም በዚህ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ እንዲገኙ በአክብሮት ተጋብዘዋል።

መጓጓዣ፡ Finchley Road Underground and Finchley Road & Frognal Rail Stations. Buses: 13, 31, 82, 113, 177, 236, 11c. ለበለጠ መረጃ፡ 07903923539 ወይም 07535217504 ይደውሉ። በ soceppuk@socepp.info ኢሜል ያድርጉልን።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ የዩኬ ቅርንጫፍ